**የርቀት ትምህርት፦ የመሠረታዊ ቴክኖሎጅ ለወላጆች/Technology Essentials**
**https://www.dpsk12.org/coronavirus/#familyresources**

**የኢንተርኔት አማራጮች፦**

- **የቤት ኢንተርኔት፦**
  - ይህ ፕሮግራም የቤት ኢንተርኔት አገልግሎትን በአነስተኛ ዋጋ የሚሰጥ ፕሮግራም ነው። የርቀት ትምህርት ፍላጎትን ከመጨመር አንጻር IE ልዩ ቅናሾችን ከከፍተኛ ፍጥነት ጋር ይዞ ቀርቧል።
  -
- **በ DPS የተሰጡ ሆትስፖቶች፦**
  - በ DPS የተሰጡ ሆትስፖቶች በቤታቸው ውስጥ የሌላቸው ተማሪዎች የተለዩ ሽቦ-አልባ አውታሮችን ለመጠቀም ያስችላቸዋል። እነዚህ ሆትስፖቶች ከስፕሪንግ እረፍት በኋላ ለሚፈልጓቸው ተማሪዎች ይታደላሉ። በእደላው ዙሪያ ተጨማሪ መረጃዎች ለት/ቤት አመራሮች ይሰጣሉ።
- **ሌሎች አማራጮች፦**
  - በዲስትሪክቱ የተለያዩ ቦታዎች መኖራቸው ታይቶ በተለያየ መጠን/ፍጥነት ተደራሽነትን ሊሰጡ የሚችሉ ሌሎች ጊዜያዊ የኢንተርኔት አማራጮች አሉ።
    - **የሞባይል ስልክ ማገናኛ (Tethering)፦** የግል ሞባይል ስልኮች እንደ ክሮምቡክ ያሉ መሣሪያዎችን ከኢንተርኔት ጋር ለማገናኘት እንደ ሆትስፖት ማገልገል ይችላሉ። ተጨማሪ ክፍያዎች ሊተገበሩ ይችላሉና ለተጨማሪ መረጃ የአገልግሎት ሰጭዎን ያነጋግሩ።
    - **የሕዝብ ዋይፋይ (Public WiFi)፦** (ተጠቃሚዎች ከዋይፋዩ ክልል በ 100 ጫማዎች ርቀት ውስጥ መሆን አለበት። ነገር ግን በዚህ በቤት ውስጥ ቆዩ የሚለው ትዕዛዝ ባለበት ወቅት ላይሠራ ይችላል። ሆኖም ግን የሕዝብ ዋይፋዮች የሌሎቹን አማራጮች ያህል ደህንነታቸው የሚያስተማምኑ ስለሆነ በጥንቃቄ መጠቀምን አስታውሱ።
      - XFinity WiFi Hotspots (በከተማው በሞላ ሽፋናቸው ይለያያል)
      - የ DPLWireless (በ DPL ቦታዎች ወይም በፓሪኪንግ ሥፍራዎችን ይሸፍናል)
      - DPS Guest (DPS ት/ቤቶች እና ፓርኪንግ ሥፍራዎችን ይሸፍናል)

**የተማሪዎችን ደህንነት መጠበቅ**

- **የ DPS ማጣሪያ፦**
  - የተማሪዎቻችን የመስመር-ላይ ተሞክሮዎች ደህንነትን የተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ DPS የሚቻለውን ሁሉ ያደርጋል። ዲስትሪክቱ በሚሰጣቸው መሣሪያዎች እና በዲስትሪክት አውታር ግንኙነቶች ላይ የተካተቱት የድር ማጣሪያዎች በተቻለ መጠን ተገቢ ያልሆነ ይዘትን እንዲያግዱ ፕሮግራም የተደረጉ ናቸው።
  - አንድ ተማሪ ዲስትሪክቱ የሰጠውን ክሮምቡክ ወይም አይፓድ በት/ቤት ወይም በቤት ከተጠቀመ ሁልጊዜም የሚያልፈው በ DPS ድር ማጣሪያ በኩል ነው።
  - እንደሁሉም በቴክኖሎጂ ላይ የተመሠረቱ መፍትሄዎች፣ ተጠቃሚዎች እነዚህን የኢንተርኔት ማጣሪያዎችን ለአልተገባ ጥቅም ለማለፍ የሚችሉባቸው መንገዶች አሉ። እናም ወላጆ የልጆቻቸውን ኢንተርኔት አጠቃቀምን እንዲከታተሉ እናበረታታለን።

- **ጸረ-ትንኮሳ (ጸረ-ቡሊንግ) ሶፍትዌር፦**
  - DPS “Docs”፣ “Sheets”፣ “Email” እና “Chat”.ጨምሮ በማንኛውም በዲስትሪክቱ በሚተዳደሩ የጉግል ምርቶች ላይ የሚካሄዱ እንቅስቃሴዎችን ለመቆጣጠር “Gaggle” ይጠቀማል። Gaggle አንዳች የትንኮሳ፣ ሳይበር ትንኮሳ ወይም ማንኛውም ሕገ-ወጥ እንቅስቃሴዎች መካሄዳቸውን ቢያሳውቅ ተማሪው ለዲስትሪክት ቴክኖሎጂው እና ተያያዥ ሶፍትዌሮች ያለውን መዳረሻ ያጣል።
- **ወላጅ ማየት ስለመቻሉ፦**
  - ወላጆች የልጆቻቸውን ኢንተርኔት አጠቃቀም ታሪክን ለማየት በመለያ መግባት ይችላሉ። ተማሪዎች በድብቅ (incognito) ሞድ ማሰስ (ኢንተርኔት መጠቀም) አይችሉም።